ኢትዮጵያዊነት፡-የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ
**ETHIOPIAWINNET:** ***COUNCIL FOR THE DEFENSE OF CITIZEN RIGHTS***
***www.ethiopiawin.net***
**ECDCR P.O Box 171, East Lansing, MI 48823**

# ኢትዮጵያዊነት የድርጅቱን እንቅስቃሴ ወደ ሀገር ቤት አዛወረ

የካቲት 26፣ 2011

**ኢትዮጵያዊነት፤ የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ** በአሜሪካ ሀገር ከተቋቋመ እነሆ አሁን ሰባትኛ ዓመቱን ይዟል ፡፡ ኢትዮጵያዊነት በአሜሪካን ሀገር በበጎ አድራጎት ድርጅትነት በሕግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ሲሆን የተመሠረተበት ዋና ዓላማው የኢህዴግ መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የዜግነት መብቶች፤ አብሮ የመኖርንና የሀገር አንድነት እሴቶች እንዲዳከሙ በማድረጉ ይህን የጥፋት መንገድ ለመከላከል የተቋቋመ የሲቪል ማኅበር ነው፡፡



With the Deputy Prime Minister, His Excellency Ato Demeke Makonnen

ድርጅታችን ተመራማሪ ምሁራኖች ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሁፎችን በዓመት አንዴ በሚያዘጋጀው ሲምፓዚየም የተገኙ አስተማሪ ዕውቀቶችን ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ለህዝብ እንዲደርስ በማድረግ፣ በኢትዮጵያ የሚከሰቱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በማሳውቅ ፣ የመብት ጥሰቱ ችግር ከፍተኛ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ ዘርና ቋንቋን ሳይለይ ዜጎችን ለዘመናት ያስተሳሰረና ወደር የማይገኝለት የአንድነት ምሰሶ የሆነው የኢትዮጵያዊነት ሥነ ልቦና በሕዝባችን እንደገና ሰፍኖ፣ በግዴታ ከተጫነበት መከፋፈል አባዜ ወጥቶ፣ በኢትዮጵያዊነት ዕሴቶቹ ተሰባስቦ፣ ፍትህና ዲሞክራሲ የሰፈነባት

ሀገር መመስረቱ ለሀገራችን የሚጠቅም መሆኑን በማመን፣ በኢህዴግ ውስጥ የታዩ ተስፋ ሰጭ ምልክቶችን ተከትሎ፣ ድርጅቱ እንቅስቃሴውን ወደ ሃገር ቤት አቅንቷል።

እ ኤ አቆጣጠር ዲሴምበር 13 2018 ዓም 4 የድርጅቱን የሥራ አመራርና 4 ሌሎች አባላትን ያካተተ በድምሩ 8 ግለሰቦችን የያዘ በዶ/ር ዕርቁ ይመር የሚመራ ቡድን ወደ ሀገር ቤት ገብቶ ተልዕኮውን ፈጽሟል። ቡድኑ በአንድ ወር ተኩል ቆይታው፤

- ከተለያዩ የተፎካካሪ ፓርቲዎች፤ ድርጅቶችና የህዝብ መብት ተሟጋች ድርጅት መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፤ ምሁራን፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣኖች ጋር ተወያይቷል፣
- በባህርዳር፤ በጎንደር፤ በወሎና በደብረ ብርሃን ዮኒቨርስቲዎች በመገኘት ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር በኢትዮጵያዊነት የጋራ ዕሴቶች ዙርያ ላይ ሰፊ ውይይቶች አካሂዷል። በሌሎች ክልሎችም ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ጋር ለመወያየት በዕቅድ ተይዟል ።
- ጥሪ ከተደረገላቸው ታዋቂ ግለሰቦችና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ጋር ውይይት አካሂዷል።
- ጥናታዊ ተልዕኮውን ካከናወነ በኋላ ስለአከናወናቸው ተግባራት ለጋዜጠኞች ገለፃ ሰጥቷል።
- በመጨረሻም ከፍ ብለው ከተጠቀሱት ስብሰባዎችና ግንኙነቶች፣ በሀገር ወዳድነታቸው፤ ከሕዝብ ጋር ባላቸው ግኑኝነትና የዕውቀት ደረጃ፣ አሥራ አንድ አባላትን ያካተተ በሀገር ቤት የሚንቀሳቀስ ጊዜያዊ የኢትዮጵያዊነት ምክር ቤት (ካውንስል) አቋቁሟል። የካውንስሉ የአጭር ጊዜ ተግባራት ድርጅቱን በሀገር ቤት ህጋዊ ማድረግና ለሚፈጠረው የኢትዮጵያዊነት ኢንስቲትዩት መሠረት መጣል ነው።
- 

Addis Abeba Meeting



With Gondar University President Dr Desalegn Mengesha.

ቡድኑ ሀገር ቤት ከገባበት ቀን አንስቶ ከሕዝባችንም ሆነ ከመንግሥት የተደረገለት አቀባበልና ትብብር ከተጠበቀው በላይ ነበር ። በአንድ ወር ተኩል ቆይታችን የሄድንበትን ዓላማ ለማሳካት መቻላችንን ስንገልጽ በደስታ ነው። ከከፍተኛ ባላሥልጣናት አንስቶ ሁሉም ወገኖቻችን የኢትዮጵያዊነት መዋቅራዊ አደረጃጀት ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን ተገንዝበናል። ኢትዮጵያዊነት በሀገሪቱ ለተከሰተው የፅንፈኛና "ዘረኝነት" ችግር ፍቱን መድኅኒት እንደሆነ አረጋግጠናል። በርካታ ወገኖች በድርጅቱ ሥር ተመዝግበው ተሳታፊ ለመሆን ፍላጎታቸውን ገልፀዋል።

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው የኢትዮጵያዊነት ኢንስቲትዩት ተመሥርቶ በመላው ሀገራችን ተስፋፍቶ ውጤት እንዲያመጣ ሀገር ወዳዶች በአንድነት መነሳት ይኖርብናል። ቢቻል በያለንበት በቤተሰብ፤ በጓደኛ፤ በእምነት ተቋማትና በሌሎችም የሶሽያል ማህበራት ጭምር ተሰባስበን ይህን የተቀደሰ ዓላማ በሰው ሀይል፤ በቁሳቁስና በፋይናንስ መርዳት ይኖርብናል።

ከድርጅታችን ጋር ለመገናኘት በሚከተሉት አድራሻዎች ብትልኩልን ይደርሰናል።

Email፤ Ethiopiawinnet@gmail.com
Website: www.ethiopiawin.net
Twitter: @Ethiopiawinnet
Postal Address: P.O. Box 171 East Lansing, MI 48823 USA

**Long live Ethiopia and Ethiopiawinnet!**